ግልጽ ደብዳቤ 24 ኖቬምበር 2009 (እ ኤ አ)

ይድረስ ለጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ 85 ሚሊዮን ደርሷል ተብሎ ይገመታል፤ ከሕዝቡ ወደ 57 በመቶ የሚሆነው ለመጠጥና ለምግብ መሥሪያ የሚሆን ውሃ እንኳን በመኖሪያው አካባቢ አያገኝም፤ ለመጸዳጃ የሚሆን ውሃ የማያገኘውማ ከ100ው 89 ይደርሳል። ከ100 ወደ 38 ያህሉ ሕዝብ ሳይጠግብ የሚያድር ደሃ ነው።ከመቶው ስምንቱ ሕጻናት አምስት ዐመት ሳይሞላቸው ነው የሚሞቱት። እነዚህ ከሞላ ጎደል ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም መሠረታዊ የሆኑትን ፍላጎቶች እንኳን የማሟላት ሁኔታ እንዳልተፈጠረለት የሚያሳዩ ናቸው።

ለምን እንዲህ ሆነ? ማን ነው ተጠያቂው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ብዙ የተለያዩም ሆነ እርስ በርስ የተያያዙ መልሶች ይኖራሉ፤ ግን በዚች አጭር መልእክቴ የማነሳው ወሳኝ ነው ብዬ የምገምተውን አንድ ነጥብ ብቻ ነው፤ ይሄውም የፖለቲካ አስተዳደርን ነው።

ባለፉት ሁሉ ዘመናት በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈራረቁት ርዕሰ-ሥልጣናት የሕዝብን ደህንነትና እድገት መአከላዊ ያደረገ ራዕይ ያልነበራቸው ገዥዎች እንጅ መሪዎች አልነበሩም። እናስተዳደርሃለን የሚሉትን ሕዝብ ሁኔታ በአለም ዙሪያ ካሉት ሕዝቦች ሁኔታ ጋር በማገናዘብ፣ የአገራቸውን ብልጽግናና እድገት ከሌሎቹ አገሮች ጋራ በማወዳደር፤ ሕዝባቸውንና አገራቸውን የአለም ሀብት ድርሻ ተካፋይ የማድረግ ጥረት ሳያሳዩ ነው ያለፉት። አገር ገዥዎች እንጅ መሪዎች አልነበሩምና። በመምራትና በመግዛት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።

መሪዎች ሕዝብን አማክረውና ፈቃደኝነቱን ጠይቀው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ብሶቱን ሰምተውና በደሉንም አጣርተው አስተዳደራቸውን ያሻሽላሉ። አስተዳደራቸው በተለያዩ ምክንያቶች ብቃት የሚጎድለው መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ አማራጭ መፍትሔ አመጣለሁ፣ የተሻለ ብቃት አለኝ ለሚል አመራር፤ ሕዝብ ኃላፊነቱን እንዲሰጥ ሁኔታውን ያመቻቻሉ።

ገዥዎች ግን ሕዝብ አጎብድዶና ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛላቸው ኃይል እስከመጠቀም ይደርሳሉ። እኛ ነን የምናውቅልህ በማለት፣ አፍነውና ጨቁነው በመያዝ በአስተዳደራቸው የማይተማመን፣ በራሱ የማያምንና እርስበርሱም የማይተማመን ያደርጉታል። በራስ ማመንና እርስ በርስ መተማመን ደግሞ ለኅብረት፣ ለአንድነትና ለተስፋ ዋና መሠረቶች ናቸው። ለሕዝብ ደህንነትና መረጋጋት፣ ለአገር እድገትና ብልጽግና መቆሚያዎች ናቸው። ይሄም በምርምርና በጥናት ተደርሶበት የተጠቀመ ከመሆኑም ሌላ፤ በዘመናችን ያደጉ ናቸው በምንላቸው አገሮች ሂደት በበቂ ተመስክሮለታል።

በዚህ አጭር ግንዛቤ ላይ የሚስማማ ሁሉ በመግቢያው ላይ ለገለጽሁት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚገኝበት ሁኔታ፤ ዋና ምክንያቱ የፖለቲካ አስተዳደር ጉድለት እንደሆነ መስማማት አይሳነውም።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆይ፤
የፖለቲካ ግንባታ ለሁሉም ግንባታዎች መሠረት ነው። የፖለቲካ ግንባታ ማካሄድ ማለት ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ ዕድል እንዲያገኙ ሁኔታ መፍጠር ማለት ነው። የመሪነት ኃላፊነት

ሊወስዱ የሚችሉ ዜጎችን ማበረታታት ማለት ነው። ምክንያቱም የመራጮችና የተመራጮች መበርከት ማለት የአማራጭ ሃሳቦችም መበርከት ማለት ነውና። ይሄ ማለት ደግሞ መሪዎች አመራራቸው ብቃት ሳይኖረው ቀርቶ፤ አገርንና ሕዝብን ያህል ትልቅ አደራ ለሚተካቸው ቡድን ወይም ግለሰብ አሳልፈው የሰጡ ዕለት፤ ያላሳብ እንቅልፍ ተኝተው ሊያድሩ ይችላሉ ማለት ነው። ወይ ደግሞ ድንገት መሪ ቢሞት አገር አብራ መሞት አይኖርባትም ማለት ነው።

የአንድ አገር ዋና ሀብት የሕዝብ ጉልበትና ዕውቀት ነው። ለምሳሌ ያህል፤ የአለምን ጥሬ ሀብትና እውቀት በመጠቀምም ሆነ በንግድ በመንሰራራት የበላይነትን ይዘው ያሉት ኃያላን አገሮች በሚቀጥሉት ሃምሳ ዐመቶች ውስጥ የሠራተኛ እጥረት ይገጥማቸዋል። ይሄም የሚሆንበት ምክንያት በእድሜው ለሥራ የሚደርሰው የሕዝብ ክፍል ከጡረተኛው ጋራ ሲወዳደር በቁጥር እያነሰ ስለሚመጣ ነው። ይህንን ኢኮኖሚያቸውን ሊያዛባ የሚችል ችግር ለመወጣት አገሮቹ እያቀዱ ያሉት ወጣትና የተማረ የሰው ኃይል ከታዳጊ አገሮች መመልመል ነው። ይሄ ለኢትዮጵያ ምን ችግር ሊያስከትል እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ችግሩን ለመከላከል፤ ዛሬ የሚሸሸውንም የሰው ኃይል ሆነ የወደፊቱንም ለማቆም፤ ኢትዮጵያን ተወላጆቿ ለመኖር የሚመርጧት አገር እንድትሆን ማዘጋጀትን ይጥይቃል።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆይ፤
ኢትዮጵያ የድህነትና የረሃብ ታሪኳን ለመለወጥ የእያንዳንዱ ተወላጅ ተሳትፎ ያስፈልጋታል። ሕዝቡ በራሱ የሚያምንና እርስ በርሱ የሚተማመን እንዲሆን የሚያበቃ ሁኔታ መፍጠር በጣም አጣዳፊ ሆኖ ባለበት ጊዜ፤ እንዴት አማራጭ አመራር እንሰጣለን፣ ላገራችን ችግሮች አዲስ መፍትሄ አለን ብለው የሚነሱ ዜጎች ብርቅ መሆን ሲገባቸው እስር ቤት ይቆለፍባቸዋል? እንዲህ ያለው እርምጃ ቀደም ብዬ የተነተንኳቸው የመሪነት ባህሪያት ውስጥም የሚካተት አይደለም።

ሆኖም ግን ታሪክን የመለወጥ ዕድሉ ገና ጨርሶ ከጅዎ አላመለጠምና እንዲጠቀሙበት እመኝለዎታለሁ። ዛሬውኑ በመሪነትና በገኘነት መሀል ምርጫ ከማድረግ የሚያግድዎት ከራስዎ በስተቀር ማንም የለም ብዬ አምናለሁ። ሁሉንም አማራጭ ሃሳቦች እንደ እድገት ምንጭ ተመልክተዋቸው፣ አገራችንን መምራት እንችላለን ብለው የሚነሱትን እንደጠቃሚ ኃይሎች አይተዋቸው የፖለቲካ ግንባታ ከሁሉም ጋር እንዲጀምሩ እመኝለዎታለሁ። የአገር ግንባታ ያለፖለቲካ ግንባታ አይሆንም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመራጭና ለተመራጭነት ማብቃትን ያህል ትልቅ ታሪካዊ አስተዋጾ የለምና ከእጅዎ አያምልጥዎት።

ከዚህ በመነሳት የሚከተሉትን ሁለት አቤቱታዎች በትህትናና በቅንነት አቀርባለሁ፤

- ብርቱካን ሚዴቅሳና ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ ይፈቱ!
- ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ያለምንም ተጽኖ ሊሳተፉበት የሚችሉት ነጻ ምርጫ ይካሄድ!

የሺወርቅ ወንድሚነህ
(የኢትዮጵያ ተወላጅ፣የአለም ዜጋ፣በስዊድን ኗሪ)